# መስፈርቶችን ከፍ ማድረግ (RAISING THE BAR)

## PARCC: የተማሪን ስኬታም ነት ለመደገፍ አዲስ ግምገማ



**የተማሪን የትምህርት ስኬታማነት ለመደገፍ የፈተነናውን መስፈርቶች ከፍ አድርገናል። በየዕለቱ፣ የልጅዎ ትምህርት፣ በስቴቱ የጋራ ዋና መሠረታዊ መስፈርቶች (the Common Core State Standards) እንዲመራ እየተደረገ ነው። እነዚህ ተፈታታኝ መስፈርቶች ተማሪዎችን ሁሉ ለኮሌጅ ትምህርት፣ ለሙያ እና ለሕይወት መሳካት ያዘጋጃሉ።**

በዚህ ፀደይ የ DC-CAS ፈተና በአዲስ የመገምገሚያ ፈተናዎች ይተካል። አዲሱ በኮምፒዩተር ላይ የተመሠረተ የ PARCC. ግም ገማ በከፍተኛ ደረጃ የሚጠበቀውን ከጋራ ዋና መሠረታዊ መስፈርት (the Common Core) ጋር የሚጣጣሙ ሲሆን፣ ተማሪዎች በጥልቅ እንዲያስቡ እና ዕውነተኛ የሕይወት ችግሮችን እንዲፈቱ ያስችላቸዋል። ከ 3–8 ተኛ ክፍል የሚማሩ እና በአልጀብራ (Al-gebra) I፣ ጂኦሜትሪ (Geometry)፣ እና እንጊሊዘኛ (English) I & II ትምህርቶች የተመዘገቡ ተማሪዎች በዚህ ዓመት የ PARCC ፈተና ይፈተናሉ። PARCC ልጅዎ በትምህርት ቤት ምን እየተማረ እንደሆነ ይገመግማል፤ እንዲሁም ተማሪዎች ለኮሌጅና ለሙያዎች መሳካት በትክክለኛው ጎዳና ላይ መሆናቸውን ማወቅ እንዲችሉ መምህራርንን እና ወላጆችን ይረዳል።

*PARCC ለኮሌጅ እና ለሙያዎች ዝግጁነት የቆመ ቃል ነው።*

## PARCC: ምን እንደሚጠበቅ

**ምን:** PARCC ተማሪዎች በኮምፒዩተር ላይ የሚፈተኑት አዲስ እና የበለጠ የላቀ ፈተና ነው። ይህ DC-CAS ን ይተካል።.

**ማን:** ከ 3–8 ተኛ ክፍል የሚማሩ እና ለአልጀብራ I፣ ጅኦሜትሪ፣ እንጊሊዘኛ I እና II ትምህርት የተመዘገቡ የዲሲፒኤስ ተማሪዎች በሙሉ (የዲሲፒኤስ እና የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች)

**መቼ:** የ PARCC ግምገማ በሁለት ምድቦች ይካሄዳል።

**ምድብ 1:በትምህርት ክንውን ላይ የተመሠረተ ( Performance-Based Assessment) ግምገማ (ንባብ እና ሂሳብ)**
ቀን፣ መጋቢት (March) 10– ሚያዚያ (April) 8, 2015

ጽሕፈትን፣ የምርምር ክህሎቶችን፣ እና በርካታ የአሠራር እርምጃዎችን የሚ ጠይቅ የሂሳብ ጥያቄዊችን፣ የተማሪውን የመሥራት ችሎታን ይገመግማል።

**ምድብ 2: የዓመቱ ግምገማ ማብቂያ (ንባብ እና ሂሳብ )**
ቀኑ: ግንቦት (May) 7– ሰኔ (June) 5, 2015

የማስተዋል ንባብን እና የሂሳብ ጽንሰ ሀሳቦችን እና ክህሎቶችን በምርጫ ጥያቄዎችና አጭር መልሶችን በሚፈልጉ ጥያቄዎች አማካኝነት ይለካል።

ማስታወሻ፣ በፈተና ሰሞን ተማሪዎች በየቀኑ አይፈተኑም ። እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ፈተና የሚሰጥባቸውን ቀናት የሚወስን ሲሆን ልጅዎ በትክክል መቼ እንደሚፈተን እንዲያውቁት ያደርጋል። ጠቅላላ የ **PARCC** ፈተና መፈተኛ ጊዜ ለእያንዳንዱ ተማሪ ልክ እንደ **DC-CAS** ፈተና ይሆናል።

### የ PARCC ግምገማ ፈተናዎች ከ DC-CAS ፈተና የሚለዩት እንዴት ነው?

| | DC-CAS | PARCC |
|---|---|---|
| ፈተና የሚሰጥባቸው ክፍሎች | 3–10 | 3–8 ክፍል ተማሪዎች<br>አልጀብራ I,<br>ጅኦሜትሪ፣<br>እንጊሊዘኛ I & II |
| የሥርዐተ ትም ህርቱ ትኩረትረት | በ መሠረታዊ ዋና የስቴት መስፈርቶች ላይ ያልተመሠረተ | በ መሠረታዊ ዋና የስቴት መስፈርቶች |
| ዓላማው | ከ K–12 የብቁነት ግምገማ | ለኮሌጅ እና ለሙያ በትክክለኛ ጎዳና ላይ መሆን አለመሆንን ይገመግማል |
| ፈተናው እንዴት እንደተሰጠ | እርሳስ እና ወረቀት | በኦንላይን (ኮምፒዩተሮች) |

PARCC ለእንጊሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች እና ግላዊ የትምህርት እቅድ (Individualized Education Program) ፕሮግራም ወይ ንም 504 እቅድ በበርካታ አቅርቦቶች አማካይነት ይስተናገዳሉ።.

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

ስለ PARCC የበለጠ መረጃ dcps.dc.gov/DCPS/PARCC. ይቃኙ